# ምርጫ እና ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን

## መጋቢት 2013 ዓ/ም

Demera Media & Communication Service PLC
ADDIS ABABA, ETHIOPIA
+251 911 057837  +251 911 488888

## ይዘት ገፅ


ምርጫ እና ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን....3

መግቢያ....3

ምርጫ፡ ምርጫ ምንድን ነው? ምርጫና ታሪካዊ አመጣጡ; ዘመናዊ ምርጫና ኢትዮጵያ? ምርጫና መገናኛ ብዙኀን በኢትዮጵያ....3

**ማህበራዊ ሚዲያ፡ የማህበራዊ ሚዲያ አነሳስ እና እድገት፡ ማህበራዊ ሚዲያና የኢትዮጵያ ፖለቲካ፣ ማህበራዊ ሚዲያና ምርጫ...**....6

**የማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን አነሳስ እና እድገት**....6

**ማህበራዊ ሚዲያና የኢትዮጵያ ፖለቲካ**....7

**ምርጫና ማህበራዊ ሚዲያ፣ የተለያዩ ሀገራት ልምዶች**....9

**ክፍል አንድ፡ ማህበራዊ ሚዲያ ለምርጫ የሚያበረክተው አዎንታዊ አስተዋፅኦ(የተለያዩ ሀገራት ልምዶች ይኖሩታል)**....11

**1.1. ምርጫን የተመለከቱ መረጃዎች በሰፊው እንዲሰራጩ ማድረግ**....12

**1.2. በእውቀት ላይ የተመሰረተ የምርጫ ተሳትፎን ማሳደግ**....13

**1.3. የመራጭ ቁጥርን ማብዛት**....13

**1.4. ከምርጫ ጋር ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ጠያቂነትን ከፍ ማድረግ**....14

**1.5. የፖለቲካ አንቂዎችን ማብቃት**....15

**1.6. ትኩረት ያልተሰጣቸው ሀሳቦች እና ድምፃች ትኩረት እንዲያገኙ ማገዝ**....16

**ክፍል ሁለት፡ ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ምርጫ ላይ የሚያሳድሩት አሉታዊ ተፅእኖ (የተለያዩ ሀገራት ልምዶች**....17

**2.1. ምርጫን የተመለከቱ የተሳሳቱ መረጃዎች እና የጥላቻ ንግግር መሰራጨት (fake news and Hate speech)**....17

**2.1.1. የተሳሳቱ መረጃዎችን ( Fake News) ማሰራጨት**....17

**2.1.2. የጥላቻ ንግግር (Hate speech)**....20

**2.2. ምርጫን እና የምርጫን ሂደት ለማስተጓጎል መሳሪያ ሆኖ ማገልገል**....22

**2.3. ከምርጫ ጋር ተያያዥ የሆኑ ግጭቶችን መቀስቀስ እና ማዛመት**....24

**2.4. የምርጫ ውጤት በህዝብ ድምፅ ሳይሆን በተሳሳተ መረጃ ስርጭት ምክንያት እንዲወሰን ማድረግ**....25

# ምርጫ እና ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን

## መግቢያ

ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን  በመጀመሪያ ሲጠነሰስ በሰው ልጅ ህይወት ላይ ይህን ያህል ዘርፈ ብዙ ተፅእኖ ይፈጥራል ብሎ ያሰበ ካለ እጅግ የላቀ አእምሮ ባለቤት መሆኑን መካድ አይቻልም። ዛሬ ላይ አለም የሚገናኝበትን መንገድ ቀስ በቀስ እየተቆጣጠረ ይምናካሂዳቸው ፖለቲካዎ ምርጫዎች ሳይቀር በማህበራዊ መገናኛብዙሀን   ጥላ ስር ወድቀዋል። በርካታ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ዛሬ ምርጫና ማህበራዊ መገናኛብዙሀን  መካከል ያለው ግንኙነት በጥንቃቄ ከስሩ፣ የተለያዩ ሀገራት ልምዶች እንደምሳሌ እየቀረቡ መጠናት እና ጥቅሙ እና ጉዳቱ ታውቆ የመፍትሄ አቅጣጫ መቀመጥ አለበት። ለዚሁ አላማ በዚህ ፅሁፍ እነዚሁ ጉዳዮች በጥልቀት ይተነተናሉ።

## 1.1. ምርጫ፡ ምርጫ ምንድን ነው? ምርጫና ታሪካዊ አመጣጡ፣ ዘመናዊ ምርጫና ኢትዮጵያ? ምርጫና መገናኛ ብዙኀን በኢትዮጵያ

እንግዲህ ምርጫ ከዋነኞቹ የዴሞክራሲያሲዊ ስርአት መገለጫዎች አንዱ እንደመሆኑ መጠን ታሪካዊ አመጣጡም ከዴሞክራሲያዊ ስርአት አመጣጥ ጋር የተያያዘዘ ነው። ህዝቦች በፍቃዳቸው እና በዴሞክራሲያዊ ስርአት በተለያየ ደረጃ ያሉ መሪዎቻቸውን የሚመርጡበት ስርአት እንደመሆኑ መጠን የሰው ልጅ በማህበር መኖር ከጀመረበት ዘመን ጀምሮ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ምርጫዎችን ሲያካሂድ ኖሯል። በምርጫ ዙሪያ የተፃፉ ድርሳናት እንደሚያሳዩት ምርጫ በምእራቡ አለም ከገናናዎቹ ግሪክ እና ሮማ ስልጣኔዎች ዘመን ጀምሮ ይካሄድ እንደነበር ያሳያሉ።

ሀገራችን ኢትዮጵያም የብዙ ሺ ዘመናት ታሪክ ያላት ትልቅ ሀገር እንደመሆኗ መጠን በየዘመናቱ እና በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ያሉ ህዝቦች የተለያዩ አይነት ምርጫዎችን ሲያካሂዱ እንደኖሩ ታሪክ ይነግረናል። የምእራባውያንን መንገድ የተከተለ ዘመናዊ ምርጫ ታሪክ ግን ከቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት ያለፈ አይደለም። በሳቸው ዘመን የነበረው ምርጫም ዴሞክራሲያዊ ስርአትን ለማስፈን የሚደረግ ሳይሆን፣ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለማስፈን ጥረት እያደረጉ ነው የሚል ስም በምእራባውያን ዘንድ ለማግኘት የሚደረግ የይስሙላ ምርጫ ነበር። ለዚህ ማሳያ ይሆን ዘንድ አንድ ጫወታ ጀባ ልበላችሁ።

ምንም እንኳን ዴሞክራሲያዊ ባይሆንም በምርጫ ፓርላማ የገቡ አባላት ጉባኤ ተቀምጠው ሳለ አንዱ ጉምቱ የፓርላማው አባል ሸለብ ያደርጋቸዋል። ወዲያው ግን አጠገባቸው ያሉ ሌላ አባል፣ "ጌታው ጌታው... ይነሱ የሳምንቱን ቃለጉባኤ ይፈርሙ" ይሏቸዋል።

"ኧረገኝ የምን ቃለጉባኤ"

"ሳምንት እዚሁ ተሰብስበን የወሰንነውን"

ለማንበብ ሳይሆን ለመፈረም እየተዘጋጁ"ኸ፣ ጥሩ፣ ለመሆኑ ጃንሆይን የሚነካ ነገር አለው? " ብለው ጠየቁ ይባላል።

ከዚህ የምንረዳው የዘመኑ ተመራጮች ውክልና ለጃንሆይ እንጂ ለህዝብ እንዳልነበረ ነው። ከዚህም የዘመኑን ምርጫ ዴሞክራሲያዊነት መገመት እንችላለን።

በደርግ ዘመንም ቢሆን ያው ምርጫ ተካሄደ እንዲባል እንጂ የመድብለ ፓርቲ ስርአት ሰፍኖ፣ ህዝብ በመረጠው መሪ የሚተዳደርበት ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመዘርጋት የሚካሄድ ምርጫ አልነበረም። ምርጫዎቹም ስርአቱ በመረጠው ጊዜ እና በመረጠው መንገድ የሚካሄድ የመንግስት እና የፓርቲ ልዩነት እንኳን በሌለበት ሁኔታ የሚካሄዱ፣ ምርጫ ለማለት የማያስደፍሩ ምርጫዎች ነበሩ።

በ1983 ዓ/ም ኢህዴግ አዲስ አበባን ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ ደግሞ በይበልጥ ዘመናዊ ምርጫ የሚመስሉ፣ አሁንም ግን በርካታዎቹን የዴሞክራሲያዊ ስርአት መለኪያ መስፈርቶ የማያሟሉ ምርጫዎች ሲካሄዱ ቆይተዋል፣ ከዘጠና ሰባቱ ምርጫ በስተቀር። በርካታ የዘርፉ ምሁራን እንደሚስማሙበት የዘጠና ሰባቱ ምርጫ ለኢትዮጵያውያን መራጮች ቢያንስ ቢያንስ ትርጉም ያለው ምርጫ የሰጠ ነበር ይባላል (ሊዮንስ፣ 2010)። ምርጫው ከፍተኛ የሆነ የተቃውሞ እንቅስቃሴ የተካሄደበት የነበረ ቢሆንም በመድብለ ፓርቲ ስርአት እንደሚደረገው፣ ስርአት ያለው ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር ማካሄድ ሳይችል ቀርቷል። በዘመኑ የነበርን ሁሉ እንደምናስታውሰው ህዝቡ ድምጼ ይከበር ብሎ በጋዜጣም በሰልፍም የሚያደርገው ትግል በኃይል እየተደፈጠጠ ማጣፊያው ቢያጥረው በሰበብ ባስባቡ፣ ለደም ልገሳም ሳይቀር "ኃይል የእግዚያብሄር ነው" የሚል ፅሁፍ የሰፈረበት ቲሸርት ማዘውተር ጀምሮ ነበር።

ከዚህ ምርጫ ኢትዮጵያ ያተረፈችው ነገር ቢኖር የዴሞክራሲያዊ ምርጫ ልምድ ነው፣ ምንም እንኳን ምርጫው ዴሞክራሲያዊ ነበር ማለት ብዙ ጥያቄዎች የሚያስነሳ ቢሆንም። ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን

ባልታወቁበት በዛ ዘመን የዴሞክራሲያዊ ምርጫ ግብአቶች ከሆኑት ጥቂቶቹን ማለትም ለህዝብ በቀጥታ የሚተላለፍ የተወዳዳሪዎች የፊትለፊት ክርክር መድረክ በማዘጋጀት፣ ለተወዳዳሪዎች የአየር ሰአት በመስጠት፣ ስለዴሞክራሲያዊ ስርአት የግንዛቤ ማስጨበጫ ቅስቀሳዎችን በማድረግ እና የማንኛውም አካል ሀሳብ በነፃነት እነዲንሸራሸር በማድረግ(በተለይ የግል ጋዜጦች) መደበኞቹ መገናኛ ብዙሀን የተጫወቱት ሚና ቀላል የሚባል አልነበረም። ነገር ግን፣ በዘመኑ ሁኔታዎችን የመረዳት እድሜ ላይ ደርሶ ያስተዋለ እንደሚረዳው፣ የምርጫው ውጤት በኃይል እንደተደፈጠጠ ሁሉ የነዚህ መገናኛ ብዙሀን ህልውናም በገዢ ፓርቲው የሚመራው የወቅቱ መንግስት ባሳደረባቸው ቀጥተኛና የእጅ አዙር ተፅእኖ ምክንያት ሊያከትም ችሏል። ጋዜጠኞቹም በአብዛኛው ለስደት፣ የቀሩትም ለእስራት እና ሙያቸውን ቀይረውና አንገታቸውን ደፍተው ለመኖር ተገደዋል።

ከ97 በኋላ በኢትዮጵያ የተካሄዱ ምርጫዎች በሙሉ ማለት ይቻላል የይስሙላ ምርጫዎች የነበሩና ገዢው ፓርቲ ባሉት ወንበሮች ሁሉ የራሱን ሰዎች መልሶ መላልሶ የሚያስቀምጥባቸው ነበሩ (ሊዮንስ፣2010)። ወደመጨረሻም 100 ፐርሰንት የደረሰ የአንድ ፓርቲ የበላይነት የታየበት ምርጫም እስከማካሄድ ተደርሶ ነበር። በ100 ፐርሰንት ድምፅ የተገኘው ስልጣን ግን ብዙም ሳይቆይ በ100 ፐርሰንት ተቃውሞ ተናጠ። ይህ በተለያዩ መንገዶች፣ በተለይም በማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን የተቀጣጠለው ተቃውሞ ዛሬ ወንበሩ ላይ ያለውን የነዶክተር አብይ አህመድን መንግስት 4 ኪሎ ቤተመንግስት አስገባ። የነበረውም ተቃውሞ ረገብ አለ፣ ምንም እንኳን በርካታ ግድያዎች እና የህዝብ መፈናቀል እንዲሁም ጦርነትን አከል የህግ ማስከበር ሂደቶችን ያስከተለ ቢሆንም።

ዛሬ ላይ ቆመን ደግሞ ሀገራዊ ምርጫ ልናካሂድ ነው እያልን ነው። በዚህ ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀኑ ዋነኛ የፖለቲካው ሰላማዊ ጦርነት መተጋተጊያ መድረክ በሆኑበት በአንዳንድ ሀገራት ልምድም የምርጫን ውጤት እስከመወሰን በደረሱበት ዘመን ላይ የማህበራዊ መገናኛ ብዙሀኑ እንዴት ይታያሉ ሚናቸውስ ምን መሆን አለበት? ነው የነገራችን ማጠንጠኛ።

## 1.2. ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን፡ የማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን አነሳስ እና እድገት፣ ማህበራዊ ሚዲያና የኢትዮጵያ ፖለቲካ፣ ማህበራዊ ሚዲያና ምርጫ

### 1.2.1. የማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን አነሳስ እና እድገት

ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን በይነ-መረብ ላይ የተመሰረተ፣ ተጠቃሚዎች መረጃን የሚያጋሩበት፣ የሚወያዩበት ፣ የሚያሻሽሉበት እና ተጋግዘው የሚፈጥሩበት ከፍተኛ እና ውስብስብ የመረጃ ልውውጥ መድረክ ነው (ኬትዝማን እና ሌሎች፣ 2011)። እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር ከ1997 ጀምሮ በርካታ የዘርፉ ጠቢባን ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ብለው ባይጠሯቸውም፣ ሰው ከጓደኛው እና ከወዳጅ ዘመዱ በቀላሉ ሊገናኝ የሚችልባቸውን የበይነ-መረብ መንገዶች ለመፍጠር ጥረት ሲያደርጉ እንደኖሩ የዘርፉ ታሪክ ያትታል (ዳና እና ኒኮል፣ 2008)።

ዛሬ ላይ በመላው አለምም ሆነ በሀገራችን ኢትዮጵያ በርካታ ተጠቃሚ ካፈሩ የማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን መካከል እንደ ፌስቡክ፣ ትዊተር፣ ዩቲውብ፣ ቴሌግራም፣ ዋትሳፕ እና ኢንስታግራም የተሳካለት የለም። በኢትዮጵያ፣ በተለይም ቀዳሚዎቹ አራቱ ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ማህበራዊ ግንኙነትን ከማሳለጥ ባሻገር፣ ለሰላማዊ አላማ ህዝብን ከማገናኘት እና ከማነሳሳት ጀምሮ፣ ሀዘተኛ መረጃ ማስተላለፍ(fake news)፣ የጥላቻ ንግግርን ማሰራጨት(hate speech)፣ ቁልፍ ሀገራዊ የድርጊት መርሀግብሮችን ማስቀየር፣ ፖለቲካዊ እና ሀይማኖታዊ ግጭቶችን መቀስቀስ፣ ብሎም መንግስት እስከመቀየር ሙከራ የደረሱ ግቦች ማስፈፀሚያ መድረኮች መሆናቸው የእለት ከእለት ኑሯችን አካል ከሆነ ከረምረም ብሏል።

ዛሬ ላይ ቆመን ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ተፅእኖ ማሳደር ከጀመሩ ከ15 ገደማ አመታት በኋላ የአለምንም ሁኔታ ስናይ የማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን በንኡስም ሆነ በአብይ ጉዳያቻችን ሁሉ እየገቡ አስተሳሰባችንን እስከመዘወር የደረሰ ትልቅ ሚና እየተጫወቱ ነው። ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን በአንድ ጊዜ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎችን በቀላሉ ማገናኘት እና ቁጥራቸው የበዛና ውስብስብ ባህሪ ያላቸው መልእክቶችን እንዲለዋወጡ ማድረግ ይችላሉ። በግንኙነት (Communication)፣ አደረጃጀት(organization)፣ ማነሳሰት (mobilization)፣ ለአመለካከት እውቅና መስጠት (validation)፣ እና የአስተሳሰብ አድማስን በማስፋት (scope enlargement) የሚሰሩት ስራ በስራ፣ በመዝናኛ፣ በትምህርት፣ በቱሪዝም፣ በፖለቲካ እ በሌሎችም ላይ ያላቸውን ተፅእኖ በከፍተኛ ፍጥነት እና መጠን እያሳደገው ነው(ሎፔዝ፣ 2014)።

### 1.2.2. ማህበራዊ ሚዲያና የኢትዮጵያ ፖለቲካ

ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀንን ለፖለቲካ አላማ መጠቀም የተጀመረው በዚህ ጊዜ ነው ለማለት ቢያስቸግርም፣ በሰፊው ግልጋሎት ላይ ሲውል ለመጀመሪያ ጊዜ የታየው ግን በ2008 የአሜሪካ ፕሬዝዳንቶች ምርጫ ወቅት ነው፡፡ የወቅቱን ምርጫ መሸነፍ የቻሉት ሁሴን ባራክ ኦባማ የምራጫ ዘመቻ ቡድን፣ ያንን ምርጫ በመደበኛው መገናኛ ብዙሀን ብቻ የቅስቀሳ ስራዎችን በመስራት ማሸነፍ አይቻልም የሚል እምነት ስለነበረው፣ በማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን የሚካሄደውን ቅስቀሳ እንደሁነኛ መላ ይዞት ነበር፡፡ በፌስቡክ፣ በትዊተር እና በዩቲውብ በተሰራው ከፍተኛ ስራ ምክንያት ኦባማ ምራጫውን ማሸነፍ ችለዋል፣ ለመሸነፋቸው ሌሎች ተጨማሪ ምክንያቶች ያሉ ቢሆንም፡፡ የናይጄሪያው መሪ ጉድላክ ጆናታን ለፕሬዝዳንትነት ለመወዳደር መወሰናቸውን ከማሳወቅ ጀምሮ በርካታ የቅስቀሳ ስራ የሰሩተ በፌስቡክ የነበረ ሲሆን የሳቸው ተፎካካሪ የነበሩት ሙሀመድ ቡሀሪም በወቅቱ የፌስቡክ ደንበኛ ነበሩ ነው፡፡ የአረብ ፀደይ ተብሎ በሚጠራው መላውን መካከለያ ምስራቅ በናጠው አመፅ ወቅት ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን የጋራ ማንነት በመፍጠር፣ በማነሳሳት እንዲሁም እንደአማራጭ የመረጃ ምንጭ በማገልገል ትልቁን ሚና ተጫውተዋል(ስፓሰጄቪክ፣ 2017)፡፡

የሀገራችንን የኢትዮጵያን የማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን በፖለቲካው ያላቸውን ሚና ስንመለከት ምንም እንኳን ዛሬም ድረስ የማህበራዊ መገናኛ ብዙሀኑ ተጠቃሚ እንደአደጉ ሀገራት ቁጥሩ የበዛ ነው ባይባልም፣ በመልካምም ይሁን በመጥፎ በሀገሪቱ በተከሰቱ ቁልፍ ቁልፍ ጉዳዮች ላይ ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ሚና መጫቸው ከጀመሩ ሰንበትበት ብለዋል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ሀገራችን ኢንተርኔትን በሚቋረጥ እና የተለያዩ ድረገፆችን በመዝጋት ትታማለት፡፡

በሀገሪቱ ከፍተኛ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ተቀጣጥሎ በነበረበት በ2018 ፣ በርካለታ የተቃውሞ ፅሁፎች፣ ምስሎች እና ቪዲዮዎች በማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ይወጡ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው፡፡ ይህንንም ተከትሎ ይመስላል ምናልባትም ከበላይ አካላት በደረሰው ትእዛዝ ኢትዮ ቴሌኮም ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀንን በተለያዩ ጊዜያት ሲዘጋ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ከመዝጋት በተጨማሪ NISS በሚል ምህፃረ ቃል የሚታወቀው የብሄራዊ መረጃና ደህንነት ኤጀንሲ ከእነዚህ ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን የሚካሄዱ ግንኙነቶችን ይሰልላል፣ ኢሜሎችን ይበረብራል፣ የአንዳንድ ግለሰቦችን እና ድርጅቶችን ድረገፆች ያግድ እንደነበር ይታወቃል ለዚህም የሚመረኮዝበት የፀረሽብር ህጉን ነው አዋጅ No. 652/2009፡፡ አፕሪል 2018

ላይ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አብይ አህመድ ስራ እንደጀመሩ ሁሉንም ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን እና ሌሎች መገናኛ ብዙሀንንም በነፃነት እንዲንቀሳቀሱ መፍቀዳቸውን ገለፁ፡፡

በኦሮሚያ የተለያዩ አካባቢዎች ከአዲስ አበባ ማስተር ፕላን እና ከሌሎች በርካታ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ፣ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግት ደግሞ በወልቃይት እና በሌሎች ጉዳዮች ምክንያት ተቃውሞዎች ተቀጣጥለው በነበሩበት ወቅት ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ከፍተኛ ሚና ተጫውተው የነበረ መሆኑ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡ የተለያዩ ሀሽታጎችን በመጠቀም ስለተቃውሞ እንቅስቃሴው በመላው አለም ለሚገኘው ኢትዮጵያው እና ትውልደ ኢትዮጵያዊ መረጃዎች ይደርሱ ነበር፡፡ የተቃውሞ እንቅስቃሴው ተሳታፊዎች ዋነኛ የሀሳብ ማንሸራሸሪያ እና ቅስቀሳ ማካሄጃ መንገድ ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ነበሩ፡፡. በመጨረሻም ገዢው ፓርቲ ለውጥ እንዲያመጣ ሊገደድ ችሏል፡፡

ምንም እንኳን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ራሳቸውም ሆኑ ሌሎች ባለስልጣናት፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ ማህበረሰብ አንቂዎች(activists) እና ህዝቡም ማህበራዊ መገናኛ ብዙሃንን ለበርካታ በጎ አላማዎች እያዋላቸው እንደሆነ ባይካድም፣ ለውጡ መጥቶ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አብይ አህመድ ስራቸውን ከጀመሩ በኋላ ሀገሪቱን ለማረጋጋት ጥረት እያደረጉ ባሉበት ወቅትም እስካሁን ድረስ ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ለበርካታ ችግሮች መቀስቀስ እና መባባስ ቤንዚን ሆነው ሲያያለግሉ እያየን ነው፡፡በአዲስ አበባ፣ በኦሮሚያ፣ በሱማሌ፣ በቤንሻንጉል እና በሌሎችም የሀገሪቱ አካባቢዎች የተነሱ ግጭቶች እና የተደረጉ አሰቃቂ ጥቃቶች መነሻም ሆነ መባባስ ምክንያት በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀንን ለእኩይ አላማ ከማዋል ጋር የተያያዘ ነው፡፡ እርግጥ ነው የሀገሪቱ ህገመንግስት እና በስልጣን ላይ የነበረው አካል ለበርካታ አስርት አመታት ሲያራምደው በነበረው የብሄር ፖለቲካ ምክንያት ዛሬ ላይ ህዝቦቸዋ ከክልላቻ በተለይ ደግሞ ወጣቱ ያለው ሀገራዊ ስሜት እጅግ የተቀዛቀዘ እንደሆነ መረዳት አይከብድም፡፡ ለዚህም ነው በምንም ምክንያት ኮሽ ባለ ቁጥር የአሰቃቂ ጥቃት ገፈት ቀማሽ የሚሆነው የአንድ የተመረጠ ብሄር አባል አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሀይማኖት ተከታይ የሚሆነው፡፡

ለዚህ የቅርብ ጊዜ ማስረጃችን የአርቲስት ሀጫሉ ሁንዴሳን አሳዛኝ ሞት ተከትሎ የተካሄዱ አሰቃቂ ጭፍጨፋዎች እና የንብረት ማውደም ዘመቻዎች ተጠቂዎችን መረጃ ማየት በቂ ይመስለኛል፡፡ በወቅቱ በማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ይሰራጩ የነበሩ የጥላቻ ንግግሮች እና ሀሰተኛ ዘገባዎች ደግሞ እሳት ላይ

ቤንዚን እንደነበሩ መካድ አይቻልም። አንደን ብሄር ጠቅሶ እገሌ ነው ሀጫሉን የገደለው ስለዚህ ተነስ፣ ታጠቅ፣ ዝመት እስከማለት የደረሱ መረጃዎች በማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ሲተላለፉ ተመልክተናል።

ከዛም በኋላ ከተካሄዱ ህግን የማስከበር ስራዎች ጋር ተያይዞ በርካታ የጥላቻ ንግግሮች እና ሀሰተኛ ዘገባዎች በማህበራዊ መገናኛ ብዙሀኑ ሲወጡ እያየን ነው። ሀገራችን በዚህ ሁኔታ ውስጥ፣ ትውልዱም በማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ላይ ጥገኛ ሆኖ እያለ ነው እንግዲህ ምርጫ ለማካሄድ እየተሰናዳን ያለነው። ህዝባችን በተለይም ወጣቱ ወደጥፋት ለመሰማራት ጥቂት የጥላቻ ንግግሮች እና ሀሰተኛ ዘገባዎች እንደሚበቁት ተረድተናል። ስለዚህም አንድም ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን በአግባቡ ከተጠቀምንባቸው ከጥፋት ይልቅ ልማትን፣ ከመጠፋፋጥ ይልቅ መዋደድን መፍጠር የሚችሉ ሁነኛ ዘዴዎች እንደሆኑ በዝርዝር ማየት ይኖርብናል። በመቀጠልም ልበ ደንዳና ሆነን፣ የለም የጥፋቱ መንገድ ይሻለናል የምንለ ከሆነ፣ እጣ ፈንታችን ምን ሊሆን እንደሚችል እንመለከታለን።

### 1.2.3. ምርጫና ማህበራዊ ሚዲያ፣ የተለያዩ ሀገራት ልምዶች

እስከቅርብ ጊዜ የነበረው ልምድ እንደሚያሳየው የዲሞክራሲ ባህላቸው በዳበረና መንግስት የሚቀየረው በምርጫ እና በምርጫ ስርአት ብቻ እንደሆነ በሚታመንባቸው በምጣኔ ሀብትም በዳበሩ ሀገራት አለማችን ከምርጫ ጋር የተያያዙ ስርአት አልበኝነቶች ይከሰታሉ የሚል እምነት አልነበራትም። ይህ ልማድ፣ ለዘመናት ሲታይ በመኖሩ ምክንያት፣ የአዳጊ ሀገራት እርግማን ብቻ ይመስለን ነበር። ዛሬ ዛሬ የምናያቸው ድርጊቶች ግን ከምርጫ ጋር ተያያዥ የሆኑ ነውጦች የመላው አለም ስጋት እንደሆኑ የሚያረጋግጡ ናቸው፣ እድሜ ለማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን፣ የጥላቻ ንግግር እና የሀሰተኛ መረጃዎች ስርጭት።

ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነን የ 2020 የአሜሪካ ምርጫ ነው። ዶናልድ ትርምፕን ነጩ ቤ ያስገባውው የ2016ቱ ምርጫም ቢሆን ከማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ተፅእኖ ነፃ ያልነበረ ቢሆንም፣ ምክንያቱም የምርጫው ተወዳዳሪዎች የሚያኮስሱ በርካታ መረጃዎች በማህበራዊ መገናኛ ይወጡ ስለነበር፣ በ2020 ምርጫ ግን አሜሪካ በታሪኳ አይታ የማታውቀው ከምርጫ ጋር የተያያዘ ስርአት አልበኝነት ለማስተናገድ ተደጋለች። በዶናልድ ትራምፕ መሸነፍ የተቆለጡ ደጋፊዎቻቸው በማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን በመደራጀት እና በጥላቻ ንግግሮች እና በሀሰተኛ መረጃዎች አስተሳሰባቸውን ሲያላሽቁ ቆይተው አንዱን ቀን የመንግስቱ ጉባኤ መቀመጫ ወደሆነው ካፒቶል ሂል የተባለ ስፍር በማቅናት ያካሄዱት መፈንቅለ መንግስት አከል እንቅቃሴ የበርካታ ንፁሀን ዜጎችን ህይወት ማሳጣቱ አንድ መት እንኳ ያልሞላው ትውስታችን ነው። በርግጥ ለዚህ ምስቅልቅል መነሻ የሆነው ዋነኛ ምክንያት የቀድሞው ፕሬዝዳንት ዶናልድ ትራምፕ ራሳቸው

ያለመታከት በማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን በተለይም በትዊተር ያካሂዱ የነበሩት የጥላቻ ንግግር እና የሀሰተኛ መረጃ ስርጭት ነው። ለዚህም ነው በመጨረሻ ትዊተር ራሱ ከእብዱን ሰው ጋር ያለውን ግንኙነት ገፃቸውን በመዝጋት የደመደመው።

በተቃራኒው ደግሞ አዳጊ ሀገር በሆነችው በኬንያ ከ2007/2008 ምርጫ በኋላ ከደረሰው ስርአት አልበኝነት እና የበርካቶች ህይወት መጥፋት ብዙ ትምህርት የተማረው የኬንያ መንግስት በቀጣይ ከተደረገው የ2013 አጠቃላይ ምርጫ በኋላ ተመሳሳይ ችግሮች እንዳይፈጠሩ በሰራው ስራ ህዝብን ከእልቂት ሊታደግ ችሏል። ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ዳዴ እያሉ በነበሩበት በ 2008፣ የተካሄደውን ጠቅላላ ሀገራዊ ምርጫ ተከትሎ በመደበኛው መገናኛ ብዙሀን እና በስልክ የፅሁፍ መልእክት ብቻ በተሰራጨ ሀሰተኛ መረጃና የጥላቻ ንግግር በኬንያ ከ 1000 በላይ ንፁሀን ህይወት ጠፍቷል(ፔንፐሉስባይትስ፣ 2015)። ያለማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን እገዛ በመደበኛው መገናኘ ብዙሀን እና በፅሁ መልእክት ብቻ ይህን ያክል ጥፋት ከደረሰ፣ ዛሬ ላይ ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን አንዲትን ትንሽ ጉዳይ ከመሬት አንስተው ሰማይ በሚያደርሱበት ጊዜ ምን ሊመጣ እንደሚችል ቀድሞ የገባው መንግስት ለማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን መተዳደሪ የሚሆን ህግ ከማበጀት አንስቶ ህብረተሰብን የማንቃት ስራ በመስራቱ ምንም እንኳን ምርጫው ከአድልዎ እና ብልሹ አሰራር የፀዳ ነበር ባይባልም የንፁሀን ህይወት በከንቱ እንዳይጠፋ ምድረግ ተችሏል።

በ2013 የኬንያ ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ተጠቃሚዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት እንዴት የጥላቻ ንግግርን፣ ጎጠኝነትን እና የሀሰተኛ መረጃን ስርጭት ለመቆጣጠር ዝግጁ ነበሩ። የሀገሪቱ መረጃና ህዝብ ግንኙነት ሚኒስቴር እንዳስታወቀው፣ አንድ ሰው አንድ ሰው የጥላቻ ንግግርን በማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ማሰራጨት ውስጥ መሰማራቱ ከተረጋገጠ 11000 ዶላር ሊቀጣ እና ሶስት አመታትን በእስር ቤት እንዲያሳልፍ ይገደዳል። ከዚህመ በተጨማሪ መንግስት ከብሄራዊ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ጋር በመተባበር በማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን የሚሰራጭን የጥላቻ ንግግርን ብቻ የሚከታተል ቡድን አቋቁሞ ትልቅ ስራ እየሰራ ይገኛል። በዚህም ምክንያት በ2013 የኬንያ ምርጫ ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን የሰጡት አገልግሎት አዎንታዊ የሆነ እና ህዝቡ በዴሞክራሲያዊ ምርጫ በመሳተፍ ተወካዮቹን እነዲመርጥ ማስተማር ላይ ብቻ የሚያጠነጥኑ ነበሩ። ይህም የሰው ህይወት እንዳይጠፋ እና ንብረት እንዳይወድም ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቷል።

እንደአጠቃላይ፣ በእድገት ደረጃቸው እና በዴሞክራሲ ስርአት ባህላቸው ሁለት ተቃራኒ ፅንፍ ላይ ያሉትን ኬንያን እና አሜሪካን እንደምሳሌ ወስደን እንዳየነው፣ አንድ ሀገር ተገቢውን ጥንቃቄ እስካላደረገች ድረስ የዳበረ ምጣኔ ሀብት ቢኖራትም፣ የዳበረ የዴሞክራሲ እና የምርጫ ባህል ቢኖራትም፣ በማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ጦስ በቅመ እና ድህረ ምርጫ ነውጥ ልትናጥ ትችላለች። ለዚህም ነው ሀገራችን ኢትዮጵያ በቅርቡ ልታካሂድ ላቀደችው ምርጫ በከፍተኛ ዝግጅት ላይ ባለችበት በአሁኑ ወቅት ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን አጠቃቀም እና አስተሳሰባችን ላይ በርካታ ስራ መሰራት አለበት የሚባለው። ከላይ እንዳየነው፣ ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን በንፅህና ለተጠቀመባቸው ፀጋን፣ እድፉን ሳያፀዳ ለገባባቸው መከራን የሚያመጡ እንደመሆናቸው ፅድቅ እና መርገምታቸውን በጥልቀት መረዳት ያስፈልጋልና ቀጥለን ሁለቱን ገፅታቸውን እንመለከታለን።

## ክፍል ሁለት፡ ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ለምርጫ የሚያበረክተው አዎንታዊ አስተዋፅ

የማህበራዊ መገናኛ በሰፊው አገልግሎት ላይ መዋል በሰው ልጅ ኑሮ እንደአጠቃላይ፣ እና የአለም ፖለቲካ ላይ በርካታ አዎንታዊ ለውጦችን አምጥቷል። በአንድ በኩል ለብዙ መቶ አመታት ትግል ሲደረግበት የነበረው የሰው ልጅ የአስተሳሰብ ነፃነት በማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ዘመን መሰናዘሪያ በማግኘቱ ምክንያት በርካታ እርምጃዎችን ወደፊት መራመድ ችሏል። ከዚሁም ጋር ተያይዞ ሀሳብን በነፃነት መግለፅ ያለማንም ኃይ ባይነት የሚተገበርበት መድረክ ሆኖ እያገለገለ ነው። የልደት እና የሰርጉን ፎቶና ቪዲዮ እዩልኝ ብሎ ከሚጋብዘው ጀምሮ፣ የቀን ውሎውን ሁሉ በቀጥታ ስርጭት ካላያችሁልኝ የሚል ሁሉ በማህበራዊ መገናኛ ብዙሀንይስተናገዳል። በሌላ በኩል ደግሞ ከመደበኛ መገናኛ ብዙሀን አንፃር ብዙም ወጪ የሌለበት የማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን መደበኛው መገናኛ ብዙሀን መደበቅ የሚፈልጉትን በተለይም ህዝባዊ አጀንዳዎችን ወደዱም ጠሉም እንዲዘግቡ ሊያስገድድ ችሏል። ምክንያቱም አንደኛ ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀኑ የመደበኛው መገናኛ ብዙሀን ምንጭ እየሆኑ ማገልገል መጀመራቸው ሁለተኛ ደግሞ እነዚህን አጀንዳዎች የማያነሱ የሆነ እንደሆን ህዝቡ እስከነናካቴው እነሱን መከታተል ትቶ ወደማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ይሄዳል የሚል ስጋት ስለተፈጠረ ነው። እነዚህን እውነታዎች በደንብ ላጤነ ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ለአለም ዴሞክራሲያዊነት ትልቅ አስተዋፅኦ እያበረከተ ነው ብሎ መደምደም ይቻላል። ምርጫን

ብቻ ለይተን አውጥተን ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ምን አስተዋፅኦ አበረከቱ ብለን ስንል በርካታ ጉዳዮችን መዘርዘር ስንችል የሚከተሉት ግን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## 2.1. ምርጫን የተመለከቱ መረጃዎች በሰፊው እንዲሰራጩ ማድረግ

ድሮ ድሮ የምርጫ ዘመቻ የሚካሄደው ጠጅ ጠምቆ፣ ሰንጋ አርዶ፣ ድንኳን ጥሎ እያበሉ እያጠጡ ነበር ይባላል፡፡ ከዛም በኋላ ደግሶ ማብላቱ መልኩን ቀየር አድርጎ ቢቀጥልም፣ ፖስተሮችን በየቦታው በመለጠፍ እና በድምፅ ማጉያ በማወጅ ይውጡና ይምረጡ ይባልም ነበር፣ ምረጡኝ የሚል የምርጫ ተወዳዳሪም እንዲሁ ያደርግ ነበር፡፡ እነዚህ ልማዶች ሙሉ ለሙሉ ባይቀሩም ዛሬ ዛሬ በማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን የሚደረገው የምረጡ እና የምረጡኝ ቅስቀሳ ትልቅ ተፅእኖ እንደፈጠረ መረዳት አይከብድም፡፡

በርካታ በጉዳዩ ላይ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ለፖለቲካዊ መረጃዎች ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ላይ ያለ ጥገኝነት በሚያስደነግጥ መጠን ጨምሯል(ጋሬት፣ 2019)፡፡ ይኸው በ2012 የተደረገ ጥናት እንደሚያሳየው፣ በከተሞች አካባቢ ከሚኖሩ አምስት ሰዎች ሁለቱ ፖለቲካዊ መረጃን በአብዛኛው የሚያገኙት ከማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ነው፡፡ ከዛም በኋላ ይህ ቁጥር በተለይ በወጣቱ ዘንድ በፍጥነት እየጨመረ መሆኑን የሚያመላክቱ ብዙ መረጃዎች አሉ፡፡

ዛሬ ዛሬ ምርጫ የሚያካሂዱ አካላትም ሆኑ የምርጫ ተወዳዳሪዎች በየሀገሩ በርካታ ተጠቃሚ ባላቸው ማህበራዊ ላይ የራሳቸውን ገፅ በመክፈት እና ታዋቂ ገፆችን በመጠቀም ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልእክት ያስተላልፋሉ፣ ትልቁን ደጋፊያቸውንም ያገኛሉ፡፡ ለዚህም ነው ምርጫ ተወዳዳሪዎችን በጣም ከሚያስጨንቋቸው ጉዳዮች አንዱ ዛሬ ዛሬ የዘመቻቸው የማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ቅስቀሳ ስትራቴጂ ነው፡፡ ጥሩ ስትራቴጂ ያላቸው ሲያሸንፉ፣ ስኬታማ ስትራቴጂ ያልነበራቸው ደግሞ ሲሸነፉ ስለታየ፣ ቢያሳስባቸው አይገርምም፡፡

በሀገራችንም ቢሆን ከገጠር እስከከተማ ቴሌቪዥን ተከፍቶ እያለ ስልኩላይ ተተክሎ የሚታይ ወጣት በበዛበት ጊዜ ምርጫ ቦርድም ሆነ ተወዳዳሪ አካላት የየራሳቸውን ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ገፅ አደራጅተው በርካታ መረጃዎችን እየሰጡ መሆናቸው አይገርምም፡፡.

## 2.2. በእውቀት ላይ የተመሰረተ የምርጫ ተሳትፎን ማሳደግ

ሁሉ ሰው ሀገራዊንም ሆነ አለማቀፋዊውን ፖለቲካዊ ጉዳይ ሁሉ እኩል ይረዳል ማለት እብለት ነው። የሰው ልጅ እንደኑሮው እና እንደስራ ጠባዩ የተለያየ አይነት አረዳድ አለው። ይህንን ማስታረቅም ቀላል አልነበረም፡ ፡ ዛሬ ዛሬ ግን እድሜ ለማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን፣ ሁሉ እየገባ የመሰለውን የሚልበት እና ይኖራለ ብሎ አስቦ የማያውቀውን ሀሳብ የሚሰማበት መድረክ በመፈጠሩ በብዙ ምህበረሰቦች እና ቡድኖች ዘንድ የሀሳብ መቀራረብ ሊከሰት ችሏል። ምንም እንኳን ይህ ሁኔታ ለእኩይ አላማ ሊውል የሚችል ሲውልም ያየነው ቢሆንም፣ አጠቃላይ ግንዛቤ የመፍጠር ሚናውን መካድ አይቻልም። በተለያየ ባህላዊ፣ ሀይማኖታዊ እና ሌሎች ውህ የማያነሱ ስህተት የሆኑ ምክንያቶች በማህበረሰቡ መገለል የሚደርስባቸው አካላት ሳይቀር የዚህ እድል ተጠቃሚ በመሆናቸው በማንኛውም ማህበረሰብ ዘንድ ያለውን በእውቀት የተመሰረተ የምርጫን ተሳትፎ ለማሳደግ ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል።

ቁድሲያ ኮንትራክቶር የተባሉ ህንዳዊት የዘርፉ ምሁር እንደሚሉት በብዙ ሀገራት ሰብሰብ ብሎ መወያየት ለሴቶች አስቸጋሪ ነው። የሴቱችን የብቻ አጀንዳ ለማራመድ በሀይማኖት ተቋማት መሰባሰብም በአካባቢው የሚቀነቀነው በዋነኝነት የወንዶች አስተሳሰብ እንደመሆኑ መጠን አስቸጋሪ ነው። ለዚህ ሁነኛ አማራጭ ሆነው የተገኙት እንደዋትሳፕ ያሉ ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ናቸው። በነዚም እየተገናኙ ሴቶች ሀሳባቸውን መለዋወጥ፣ ምርጫም ሲሆን ምን አይነት የፖለቲካ አጀንዳ የሚያራምድን አካል መምረጥ እንዳባቸው ይወያያያሉ። በዚህም ምክንያት በእውቀት የተመሰረተ የምርጫ ተሳትፏቸውን ማሳደግ ይችላላሉ።

## 2.3. የመራጭ ቁጥርን ማብዛት

አንድ ሊካድ የማይችለው ሀቅ ዛሬ ዛሬ፣ ከሊቅ እስከ ደቂቅ ፣ በርካቶች የማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ተጠቃሚ ሆነናል። ፖለቲከኞች እና ምርጫ አከናዋኞች ደግም ይህንን ጠንቅቀው ያውቃሉና የምረጡኝም ሆነ የምረጡ ዘመቻዎች በዋነኝነት እየተካሄዱ ያሉት በነዚሁ ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ሆኗል በዚህም ምክንያት ወደድንም ጠላንም ምርጫን የተመለከቱ ማስታወቂያዎችን ለማየት እንገደዳለን ይህም ወደምርጫ እንድንሄድ ያነሳሳናል። ፎርብስ የተባለው ታዋቂ መፅሄት ባወጣው አንድ ፅሁ ላይ እንዳተተው በማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ምክንያት ነው በርካታ ወጣቶች ባልተለመድ ሁኔታ መደምርጫ መሄድ የጀመሩት ብሏል፡ ፡ በአሜሪካን ሀገር ለምርጫ የተመዘገቡ ወጣቶች ቁጥር ከ2016 አንፃር ሲታይ በ2020 ው ምርጫ ከእጥፍ በላይ ጨምሯል። ለዚህም ምክንያቱ በአለማችን በተከሰተው የ ኮሮና በሽታ ወረርሽኝ ምክንያት ባልተለመደ

መልኩ ህዝቡ የማህበራዊ መገናኛ ተጠቃሚ በመሆኑና በዚህም ምክንያት ስለምርጫ ብዙ ስለሰማ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል።

የዘርፉ ባለሙያዎችም እንዳረጋገጡት ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን እንዳጠቃላይ በምርጫ እና ከምርጫ ጋር ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች በማስተባበር፣ በምዝገባ፣ እና ቀድሞ በመምረጥ የሚሳተፈው ሰው ቁጥር አጅጉን ጨምሯል።

ብዙ ግዛቶች ሪከርድ የሰበረ የመራጮች ምዝገባ ማካኼዳቸውን የዘገቡት በ2020 ምርጫ ወቅት ነው። ምንም እንኳን ለዚህ መነሳሳት ሌሎች ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩም አንዱ እና ዋነኛው የህብረተሰቡ ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ላይ ያለው ከፍተኛ የምርጫ የመሳተፍ እንቅስቃሴ ነው። በዩኒቨርስት ኦፍ ሜሪላንድ የመረጃ ጥናቶች ኮሌጅ ፕሮፌሰር እና የማህበራዊ መገኛና ብዙሀን ጥናት ባለሙያ የሆኑት ዶክተር ጄን ጎልቤክ እንዳሉት ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ላይ ላለ ለማንኛውም ሰው የምረጡ ማስታወሻዎችን እና ማበረታቻዎችን አለማየት ፈፅሞ የሚታሰብ አይደለም። ቀጥለውም ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን አንድን አካል እንድንመርጥ የሚቀሰቅሱትን ያክል እንደአጠቃላለይ ሰው ወደምርጫ እንዲሄድ እና እንዲመርጥ የሚያሳድሩት ተፅእኖ ቀላል አይደለም።

በአፍሪካም ሆነ በሀገራችን በኢትዮጵያም በመግቢያችን እንደተመለከትነው የማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን አጠቃቀማችን እያደገ ስለመጣ እና ወጣቱ ትውልድ እንደአሜሪካውያኑ ሁሉ በማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ከፍተኛ ተሳትፎ ስላለው ምርቻን የተመለከቱ መረጃዎችን በዛው ማግኘቱ አይገርም ። ሰሞኑን እየታዘብን እንዳለውም በጎም ሆነ እኩይ በርካት መረጃዎች በማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን እየወጡ ነው። እነዚህም በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ህዝቡ ወጥቶ ድምፁን እንዲሰጥ ማድረጋቸው ከአለም ልምድ ያየነው ነው።

## 2.4. ከምርጫ ጋር ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ተጠያቂነትን ከፍ ማድረግ

በፖለቲካ፣ በፖለቲካ መሪዎች እና በጋዜጠኞች፣ እንዲሁም በህዝቡ መካከል ያለውን ግንኙነት በማሳለጥ ረገድ የማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ጉልበት እየጨመረ መጥቷል። ፈጣን ለሆነ የፖለቲካ ውይይት እና ክርክር ሰፊ የሆነ እድል ፈጥረዋል። ጥናቶች እንደሚያሳዩት፣ የሰዎች ለማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ያላቸው ቅርበት በፖለቲካው ስርአት ያላቸውን እምነት በማሳደግ እና በፖለቲካ ተሳትፏቸው ላይ አዎንታዎ ተፅእኖ አለው (ጊል ደ ዙኒጋ እና ሌሎች፣ 2010)። ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ሰዎችን በጥሩ ሁኔታ እንዲደራጁ እና ተፅእኖ እንዲዲያሳድሩ እድሉን ይፈጥርላቸዋል። ስለዚህም የፖለቲካ መሪዎች ዛሬ ዛሬ ለጥፋቶቻቸው በማህበራዊ

መገናኛ ብዙሀን ምክንያት ከቀድሞው በላቀ መንገድ ተጠያዊ ሲሆኑ እናያለን ምክንያቱም ድርጊቶቻቸው በማይቋረጥ የማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ክትትል እና ግምገማ ስር ናቸውና ነው።

በቅርብ ጊዜ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥም እያየን ያለነው፣ አንዳንድ መደበኛው መገናኛ ብዙሀን ማውጣት የማይችላቸው ወይም የማይደርስባቸው መረጃዎች በማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ስለሚወጡ፣ የፖለቲካ መሪዎች እንደቀድሞው ጊዜ በሰፊው መዋሸት እየቻሉ አይደለም። አንዳንድ ለዘመናት ተደብቀው የኖሩ ሚስጥሮችም በነዚሁ ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ሲወጡ እያየን ነው። ስለዚህም በተወሰነ ደረጃ ስራቸውን፣ ከምርጫ ጋር በተያያዘም የውድድሩ ሜዳ በአንፃራዊነት ለሁሉም እኩል እንዲሆን በሚደረገው ጥረት ውስጥ የማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ሚና ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም (አብረሀም ፈቀደ፣ 2020)።

## 2.5. የፖለቲካ አንቂዎችን (Activists) ማብቃት

መደበኛው መገናኛ ብዙሀን ዋነኛው የፖለቲካ መረጃ ምንጮች ሆኖ ኖሯል። ይህ መረጃ በዋነኝነት ከፖለቲካ አዋቂዎቹ ማለትም ከመገናኛ ብዙሀን፣ ፖለቲካ ፓርቲዎች/የምርጫ ተወዳዳሪዎች፣ ወደህዝቡ የሚሄድ ነው። ነገር ግን በሀያ አንደኛው ክፍለዘመን ህዝበ ራሱ መረጃን ከባለሙያዎች እና እርሱ በእርሱ መለዋወጥ የሚችልበትን እድል በመፍጠር ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ይህንን ሁኔታ ቀይረውታል።

ዛሬ ህብረተሰቡ መረጃ ለማግኘት፣ ከራሱ ጋር ተመሳሳይ ሀሳብ ካለው ጋር ለመገናኘት፣ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ለመወያየት እና ለመከራከር፣ የፖለቲካ ቪዲዮዎችን ለመመልከት እና ለመጫን፣ የፖለቲካ አጀንዳዎችን ለማራመድ፣ የማህበረሰብ አንቂ ሆኖ ለማገልገል፣ እንዲሁም ለፖለቲካዎ ሁኔታዎች አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀንን ይጠቀማል። ስለዚህ ህብረተሰቡን እንደ ህዝብ ብቻ ሳይሆን እንደ ማህበረሰብ አንቂ ራሱን ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀንን ተጠቅሞ እያበቃ ነው ማለት ነው።

ተመራጮችም ቢሆኑ፣ መራጮችን በቀጥታ ለማግኘት፣ ፖለቲካዊ ጠቀሜታ ያላቸው እንቅስቃሴዎቻቸውን የሚያሳዩ አዳዲስ ቪዲዮዎችን እና ምስሎችን የፖለቲካ ፍላጎት ባላቸው አካላት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣ ተቃዋሚዎቻቸውን ለማጥቃት፣ ድጋፍ ለማሰባሰብ፣ ገንዘብ ለማሰባሰብ፣ እንዲሁም አንዳንድ ቁልፍ ዜናዎችን/ ማስታወቂያዎችን ለምሳሌ ያክል አብሯቸው ለምክትል ፕሬዝዳንትነት የሚወዳደረውን/ የምትወዳደረውን ለመጀመሪያ ጊዜ ለማሳወቅ ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀንን ይጠቀማሉ።

የማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ተጠቃሚ የሆነ ሰው፣ የፖለቲካም ሆነ ሌላ መረጃለማግኘት፣ አንድ አቅጣጫ ብቻ ይዘው የሚሰሩ የብዙሀን መገናኛዎች ለይ ጥገኛ አይሆኑም። ከሚግቧቧቸው ሰዎች ጋር በሚያደርጉት የፊት ለፊት ንግግር ብቻም የተወሰኑ አይደሉም። ውስብስብ በሆነ የማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን መድረክ ፅሁፎችን፣ የድምፅ መልእክቶችን፣ ቪዲዮዎችን ፣ቡድኖችን እና ሌሎችንም ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን የሚያመቻቻቸውን መንገዶች በመጠቀም መረጃን ውስብስብ በሆነ መንገድ ከተለያየ አቅጣጣ በሚያይ መልኩ ያገኛሉ። ለዚህም ነው ዛሬ ዛሬ ብዙ ሰው ከፖለቲከኞች በቅርባቸው ካሉ ፖለቲካው በደንብ ከገባቸው ሰዎች እኩል ግንዛቤ ሊኖረው የቻለው እና ሌላውንም ለማንቃት ሲበቃ የምናየው። (ጀምስ ፖንደር፣ 2018)

## 2.6. ትኩረት ያልተሰጣቸው ሀሳቦች እና ድምፃች ትኩረት እንዲያገኙ ማገዝ

ቀደም ባለው ጊዜ አንድ ሰው በብዙዎች በተለይም በመንግስት ባለስልጣናት ትልቅ የሚባል ሀሳብ ይዞ ካልሆነ በስተቀር, የመገናኛ ብዙሀን ዘንድ ደርሶ ሀሳቡን ለሌሎce ማጋራት፣ በምርጫም ተወዳድሮ ማሸነፍ የሚታሰብ ጉዳይ አልነበረም። ዛሬ ግዜ በምንም ጉዳይ ቢሆን ሰዎች ተሰባስበው የጋራ አጀንዳቸውን በመላው አለም ማስተዋወቅ ችለዋል። ለዚህም ነው ማህበራዊ መገናኛብዙሀን ዛሬ በርካታ የማህበራዊ መገናኛብዙሀን ቡድኖች ተመስርተው ርእስ ሆነው የብዙዎች መነጋገሪያ ይሆናሉ ብለን አስበናቸው የማናውቅ ጉዳዮች የብዙሀን መነጋገሪያ ሲሆኑ እያየን ያለነው። የእንቁላል አምራቾች የማህበራዊ መገናኛብዙሀን ቡድን መስርተው የእንቁላልን መልክ ቀላ ወይም ነጣ ስለሚያደርገው ምክንያት ከረር ያለ ክርክር ሲገጥሙ ስናይ ማስተዋል ያለብን ሀሳብን የመግለፅ መድረኩ መመቻቸቱ ላይ እንጂ የምንበላው እንቁላል ቀላ አለ ነጣ አለ ህይወታችንን የሚቀይር ጉዳይ ላይሆን ይችላል። ይህ የማህበራዊ መገናኛብዙሀን ገፅታ በተለይ በየሀገሩ ያሉ ትኩረት ያልተሰጣቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ድምፃቸውን እንዲያሰሙ ትልቅ አገልግሎት ሰጥቷቸዋል።

ለዚህ አጀንዳ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ዛሬም ድረስ መፍትሄ ያላገኘው በአሜሪካን ሀገር ያለው ዘርን መሰረት ያደረገ ጭቆና ማሳያ የሆነው የጆርጅ ፍሎይድ ግድያና ተከትሎ የመጣው ለውጥ ነው። ግድያው የአለምን ህዝብ ያነሳሳ ጉዳይ ሆኖ ፣ ተፅእኖውም በአሜሪካ ምርጫ ላይ እንዲሁም ዛሬም ድረስ በተለይ በእግር ኳስ ሜዳዎች ላይ እየታየ ነው ያለው። ከዚህ በፊት ፖሊስ ጥቁር አሜሪካውያ ላይ ያደረሳቸው እና ህዝብ ያወቃቸው ግድያዎች ካሳደሩት በላይ እንቅስቃሴው ለየት ያለ ስሜት የፈጠረ ነበረ። ዛሬ፣ ማህበራዊ መገናኛብዙሀንን በመጠቀም፣ ጥቁሮች እና ጉዳዩ ያገባናል ያሉ ሁሉ ባደረጉት ጥረት፣ በአሜሪካን ሀገር ያለውን መዋቅራዊ የሆነ ዘረኝነት እና ጭቆና አለም እንዲያውቀው ማድረግ ችለዋል (ማሜ አሳንቴ፣ 2020)

። ይህም በ2020 የአሜሪካ ምርጫ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ በማሳደሩ ምክንያት በዘረኝነታቸው የሚታወቁት ዶናልድ ትራምፕ በምርጫው እንዲሸነፉ ካደጓቸው ምክንያቶች አንዱ ይኸው እንደሆነ ይታመናል።

## ክፍል ሶስት፡ ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ምርጫ ላይ የሚያሳድሩት አሉታዊ ተፅእኖ

ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን በምርጫ ጉዳይ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ የሚባለው አንድም ይዘታቸው ምንም ሊባል በሚችል ደረጃ ቁጥጥር የማይደረግበት፣ መሰረተ ቢስ፣ ይህ ነው የሚባል ስርአት የሌለው፣ መሰዳደብ እና ፅንፈኝነት የበለጠ ድምፅ የሚያገኝበት፣ የተለያዩ ሀሰተኛ ትርክቶች እና ሀሰተኛ ማንነቶች ተፈጥረውበት በርካታ እኩይ የመረጃ ልውውጦች የሚካሄዱበት መድረክ በመሆኑ ነው። እንግዲህ ሀገራችን ኢትዮጵያ በበርካታ ችግሮች በተለይም በአክራሪ ብሄርተኝነት ችግር እየታመሰች ባለችበት በዚህ ወቅት ምርጫ ልታካሂድ ነው። ከላይ በመግቢያችን የተዘረዘረው የሀገራችን ሁኔታ እና ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ይህን ሁኔታ ተንተርሰው ግጭትን ለማነሳሳት፣ ለማባባስ እና የሰው ህይወት እንዲጠፋ እንዲሁም ንብረት እንዲወድም ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክተዋል። ዛሬ ላይ በመድብለ ፓርቲ ምርጫ፣ ፓርቲዎች ለሀገር እና ለህዝብ የሚበጅ የምጣኔሀብት፣ የትምህርት፣ የስራፈጠራ እና የመሳሰሉ ወሳኝ ጉዳዮች ላይ ለውጥ ለማምጣት አልመው ተወዳድረው የሀገራችን መፃኢ እድል ይወሰናል ብለን በምናስብበት ጊዜ፣ በየማህበራዊ መገናኛ ብዙሁኑ እያየነው ያለነው ወግ የሚነግረን የምርጫው አንድና አንድ አጀንዳ የራስን ብሄር የበላይነት የማስጠበቅ ጥረት እንደሆነ ነው። ይህ በጥንቃቄ ያልተያዘ እንደሆን ወዴት ሊያመራ ይችላል ብለን ስንጠይቅ የሚከተሉትን እናገኛለን።

### 3.1. ምርጫን የተመለከቱ የተሳሳቱ መረጃዎች እና የጥላቻ ንግግር መሰራጨት (fake news and Hate speech)

#### 3.1.1. የተሳሳቱ መረጃዎችን ( Fake News) ማሰራጨት

ሰውየው ጊቢው ውስጥ ያለ መናፈሻ ውስጥ አረፍ ብሎ መፅሀፍ ማንበብ ፈልጓል። ነገር ግን የሰፈሩ ጎረምሳች አጥሩ ጥግ ኳስ እየተጫወቱ እና ከጣራ በላይ እየተጯጯሁ ሰላም ይነሱታል። በከዚህ በፊት ልምዱ እንዲሚያውቀው አስፈራርቶም ሆነ አባብሎ ዞር እንዲሉለት ሊያደርግ አይችልም። አሰብ አደረገና እኚህ ትላንት የተወለዱ ልጆችማ አይጫወቱብኝም ብሎ ወጣና እንዲህ አላቸው።

"እኔ ምላችሁ፣ ላዩን መኃል ከተማ ከንቲባው ቸኮሌት እያደሉ መሆኑን አልሰማችሁም እንዴ እዚህ ቅሪላ የምታለፉት?" ይላቸዋል።

"አይ፣ አልሰማንም።" ይመልሱለታል።

"ታዲያ ምን ትጠብቃላችሁ?! መፍጠን ነዋ! ማለዳ ጀምሮ እኮ ነው በፌስታል በፌስታል ሲያድሉ የዋሉት።"

ይላቸዋል።

ያሁሉ አንድ ባታሊዮን ወጣት፣ በሰውየው ንግግር ፈፅሞ ባለመጠራጠር፣ እየተሯሯጠ ወደተባለው ስፍራ አመራ። ሰውየውም መልካም እረፍት አድርጎ መፅኀፉን መንበቡን ጀመረ።

ነገር ግን ጥቂት ቆይቶ በጣም ብዙ ሰዎች ወጣቶቹ ቸኮሌት ሊቀበሉ ወደሄዱበት አቅጣጫ መትመም ጀመሩ፡ ፡ ሰውየውም ጆሮውን ባለማመን አቅንቶ ሲያዳምጥ ቆየና ለማረጋገጥ ወጣ አለ።

እንደሰማው የሀገሩ ህዝብ ሁሉ የሚተመው እሱ ቸኮሌት ይታደልበታል ወዳለው ስፍራ ነው። አንዱን ተጓዥ አስቆመውና፣ "ይቅርታ ወዳጄ፣ ዘመቻው ወዴት ነው?" ብሎ እንደዋዛ ጠየቀው። ተጠያቂውም ጆሮውን ባለማመን "ምነው ጌታው፣ ሀገር ሁሉ ሰምቶ የጨረሰውን ነገር ሚጠይቁኝ ? አሁን ማን ይሙት ከንቲባው ከፈረንሳይ ሀገር የመጣ መልክ የሚያሳምር፣ እድሜ የሚቀጥል፣ መልካም ቸኮሌት እያደሉ መሆኑን አልሰሙም?" አለው።

ጆሮውን ማመን አልቻለም። ራሱ እንደዋዛ ፈጥሮ ያወራው ነገር እንዲህ ተቀያይሮ ህዝብን ማነቃነቁን እና ዞሮ ለራሱ መድረሱን እያሰበ ንባቡን ለመቀጠል ተመልሶ ገባ። ሆኖም ግን ከደቂቃ ደቂቃ የሚተመው ህዝብ ቁጥር ሲጨምር አንድ ጥርጣሬ አደረበት። "ማን ያውቃል ምናልባት ከንቲባው እኮ ቸኮሌት እያደሉ ሊሆን ይችላል።" ሲል አሰበና መፅሀፉን አጥፎ ህዝቡን ተቀላቀለ። መፅሀፋችንን አጥፈን ህዝብን ከመቀላቀል ይሰውረን!

ሀሰተኛ መረጃ ማለት እንግዲህ ይህ ነው፤ ሰዎች አንዳች እኩይ አላማቸውን ለማሳካት ሆን ብለው የሚፈጥሩት እና የሚያሰራጩት መረጃ ማለት ነው። ሀሰተኛ መረጃ አላማው ሰዎችን ለአንዳች እኩል አላማ ማሰለፍ(Manipulation) ሆኖ ሀሜቶችን፣ ውሸቶችን፣ conspiracy theories፣ ድርጊቶችን እና ባህሪዎችን እውነተኛ አድርጎ ማቅረብ ሲሆን ታሪኩም ከሰው ልጅ የተግባቦት(Communication) ታሪክ ጋር ተያይዞ የሚመጣ ነው (Oxford Advanced Learners Dictionary, 2018)።

ቃሉ ከፍተኛ እውቅና እያገኘ የመጣው ግን በእንግሊዝ ሀገር በተደረገው ከአውሮፓ ህብረት የመውጣት (Brexit referendum) ምርጫ እና ከአሜሪካው የ2016 ምርጫ በኋላ ነው። የሀሰተኛ መረጃ ስርጭት የነዚህን ሁለት ምርጫዎች ውጤት በመወሰን ረገድ ትልቅ ሚና ተጫውቷል ተብሎ ይታመናል(ጌልፈርት፣ 2018)። እንግሊዞቹ ከአውሮፓ ህብረት ያተረፍነው ነገር በስደተኞች መወረር ነው የሚል ሀሰተኛ ትርክት በስፋት ሲቀባበሉ በየማህበራዊ መገናኛብዙሀን ው የምርጫ አጀንዳ አድርገው አራገቡት። የህብረቱን በርካታ ትሩፋቶች ማስተዋል አቃታቸው። ዛሬ ላይ ብዙዎች ተሳስተናል ያሉበትን የፍቺ ምርጫም አካሄዱ። በውጤቱም በወቅቱ የተደሰቱበትን ዛሬ ላይ ቆመው ሲያስቡት ግን የሚፀፀቱበትን ውሳኔ ወሰኑ፣ የፈሰሰ ውሀ አይታፈስም ሆነባቸው።

አሜሪካውያኑም ቢሆኑ በዝነኛው ዛሬ ላይ ቀድሞ የሆኑት ፕሬዝዳንት ትራምፕ መሪነት በግልፅ አሜሪካ የነጮት ናት ውስጡን ሲመረምሩት ደግሞ በተለይም የነጭ ወንዶች ብቻ ናት የሚል ትርክት በማሰራጨት፣ በስም እየጠቀሱ ነጭ ያልሆነውን ዘር ሁሉ ፀያፍ ቅጥል ስም እየሰጡ የምርጫ ቅስቀሳቸው ዋነኛ ማጠንጠኛ አደረጉት። ምጣኔ ሀብታችንን የጎዱት፣ ስራህን የሚወስዱብህ እነሱ ናቸው ብለው ሰበኩ፤ በዚህም ተሳክቶላቸው ፕሬዝዳንት ሆኑ። የስልጣን መንበሩን እንደተቆናጠጡ ግን ሀገር በእድገት መንገድ ከመምራ ይልቃ ያንኑ የሞኝ ለቅሷቸውን ሲደጋግሙ ህዝብ አንቅሮ ተፋቸው ብዙም ባልተለመደ መልኩ የአንድ የምርጫ ጊዜ(one term)ፕሬዝዳንት ሆነው ከነጩ ቤተ በውርደት ተሰናበቱ።

የሀሰተኛ መረጃ ትልቁ አደጋ የሰው ልጆችን እንደአበደ ውሻ የሚያንቀዠቅ እና የሚያናክስ መሆኑ ነው። በዚህም ምክንያት በሀገራችን በኢትዮጵያም ሆነ በበርካታ የአለማችን ሀገራት በርካታ ዘግናኝ ጥፋቶች ደርሰዋል እየደረሱም ነው። እንዲህ የሚባለው ብሄር፣ ሀይማኖት ወዘተ አባላት የኛ ብሄር፣ ሀይማኖት ወዘተ ላይ እንዲህ አደረጉ የሚል የሴራ ትርክት ይፈጠርና ብዙ ጊዜ ሰዎች ከሚወዷቸው፣ ከሚያምኗቸው፣ የኛ ብሄር አባል ከሚሏቸው፣ የኛ ሀይማኖት ተከታይ ከሚሏቸው፣ ወይም "የኛ ሰፈር ልጆች" ከሆኑ ወዳጆች ይሰማሉ። ይህንንም ይዘው በርካቶች ገጀራና ጠመንጃ ይዘው የተባለው ብሄር፣ ሀይማኖት ወዘተ አባላት አሉ ወደሚባልበት የሚተሙበት ዘመን ላይ ነው ያለነው። በምርጫ ወቅትም ቢሆን በጣም የተለመደው ነገር እገሌ የሚባለው ብሄር አባላት፣ ፓርቲ፣ ግለሰብ እና ሌሎችም እንዲህ ሊያደርጉ አስበዋል የሚል መረጃም ሆነ ማስረጃ በሌለው እንደው ብቻ የሆነ የማይጨበጥ የመረጃ ጭላንጭል ተይዞ የምርጫ ሀሳብ ሲቀያየር እንዲሁም ሰዎች ወደ ጠብ እና ጥፋት ሲያመሩ በተደጋጋሚ ታይቷል። ለዚህም ነው ዛሬ ላይ ቆመን ስለምርጫ ስናሰብ ሁላችንም ቆም ብለን፣ ለምርጫ ውሳኔዎቻችንም ሆነ ለተያያዥ ውሳኔዎቻችን

መነሻችንን መሰረት ያለው መረጃ እና ማስረጃ እንጂ ሀሰተኛ መረጃ አለመሆኑን ማረጋገጥ ትልቅ ትኩረት ልንሰጠው የሚገባ የራሳችንንም ሆነ የሌሎችን ህይወት ሊቀይር የሚችል ጉዳይ ነው።

ለዚህም ነው በርካታ የአለማችን ሀገራት የሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን የሚቆጣጠሩበትን ህግ በማውጣት ላይ የሚገኙት። ጣልያን፣ ፊሊፒንስ፣ አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ እስራኤል፣ እና ሌሎች ሀገራት የሀሰተኛ መረጃ ስርጭት ህግ ረቂቆቻቸውን ከመፅደቅ ለጊዜው ያዘገዩ ቢሆንም እንደ ጀርመን፣ ህንድ ፣ ካናዳ፣ ኳታር ፣ ኢንዶኔዥያ፣ ቼክ ሪፐብሊክ፣ እና ፊንላንድ የመሳሰሉ ሀገራት ደግሞ ህጋቸውን አውጥተው ወደስራ ገብተዋል።

እነዚህ ሀገራት በርካታ ከሀሰተኛ መረጃ ስርጭት ጋር ሊነካኩ የሚችሉ አካላትን የቴክኖሎጂ ኩባንያዎችን፣ የድረገፅ አስተዳዳሪዎችን፣ የኢንተርኔ አገልግሎት ሰጪዎችን፣ እና ሌሎችንም በስራቸው የሀሰተኛ መረጃ ስርጭት የገባ እንደሆነ ቅጣት እንደሚከተላቸው እያስገነዘቧቸው ነው። ለአብነት ያክል በጀርመን ሀገር በህግ ያልተፈቀደን መረጃ ለህዝብ ያቀረበ የቴክኖሎጂ ኩባንያ በ24 ሰአት ውስጥ ያላወረደ እንደሆነ፣ 50 ሚሊየን ዩሮ ይቀጣል።

በአፍሪካም ከበርካታ አስከፊ ልምዶቻቸው በመማር በርካታ ሀገራት ህግ እያወጡ ወደተግባር እየገቡም ነው። ኬንያ ይህንኑ ጉዳይ የሚዳኘውን የኮምፒውተር እና ሳይበር ህግን በ2018 አውጥታ ወደትግበራ ገብታለች። ኢትዮጵያም ብትሆን ተመሳሳይ ህግ ለማውጣት በሂደት ላይ ነች። ይህ ማለት ግን በሀገራችን የሀሰተኛ መረጃን ማሰራጨት አያስቀጣም ማለት አይደለም፣ ሌሎች ለተመሳሳይ ወንጀሎች ቅጣት የሚሆኑ በርካታ ህጎች እንዳሉን ግልፅ ነውና እነሱ ይተገበራሉ።

ይህ ሁሉ የሚያሳየው አለም የሀሰተኛ መረጃን ስርጭት አደገኛነት እየተረዳ እርምጃም እየወሰደ መሆኑን ነው። ለነገሩ ጥንትም ቢሆን ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው ይባላልና በወሬ ላለመፈታት ሰከን ብለን መረጃን ?"እንደሚያወጡ ካመንባቸው ምንጮች መገኘቱ፣ ምክንያታዊ እና ሚዛናዊ በመሆኑ ነው። ከምንወዳቸው፣ ከምናምናቸው፣ የኛ ብሄር አባል ከሆኑ፣ የኛ ሀይማኖት ተከታይ ከሆኑ፣ ወይም የኛ ሰፈር ልጆች ከሆኑ ወዳጆቻችን ስለመጣ አይደለም።

### 3.1.2. የጥላቻ ንግግር (Hate speech)

"በዲቪ ምናምን ሰበብ፣ ለምንድን ነው ከእነዚህ ... አፍሪካ ሀገራት ሰው የምናመጣው? ለምን እንደኖርዌይ ካሉ አሪፍ ሀገራት አናመጣም ?" ትራምፕ ጠየቁ።

ረዳታቸው አቅማማ " እነሱማ እኮ ወደኛ መምጣት አይፈልጉም?"

"ደግሞ ምንድን ነን ብለው ነው ወደ ታላቂቱ ሀገር ወደ አሜሪካ መምጣት የማይፈልጉት?" ትራምፕ በንዴት ጠየቁ።

"ስለሚበልጡን ነው ክቡር ፕሬዝዳንት፣ ይበልጡናል እነኖርዌይ።"

"እንዴት ተደርጎ! አንት ደፋር! "ተናደዱ ትራምፕ። "ከኛ የሚበልጥ ሀገርማ የለም እስኪ በምን በለጡን?"

አሰብ አደረገና "ለምሳሌ ያክል፣ በአጠቃላይ የህክምና መድን ጌታዬ። እነሱ ለሁሉም ዜጋ አጠቃላይ የጤና መድን ከሰጡ ቆዩ፣ እርስዎ ግን ይቃወሙታል ይመስለኛል።"

"ከሰደበኝ የነገረኝ" ነውና እኛን አፍሪካውያንን ለመግለፅ የተጠቀሙበትን ስድብ እኔ አልደግመውም። ለትራምፕ ከአሜሪካ የሚበልጥ ሀገር የለም እነኖርዌይ ተከታዮቻቸው ናቸው። ነገር ግን ረዳታቸው እንደነገራቸው ሁሉ እንደትራምፕ አይነት የእውቀት እጥረት ያለባቸው እና አንዳች እኩይ አጀንዳ ይዘው የሚንቀሳቀሱ አካላት የሌሎችን ስም በማጠልሸት የራሳቸውን አላማ ለማሳካት ሲጥሩ የጥላቻ ንግግርን(Hate speech) ይፈጥራሉ።

የትራምፕን የጥላቻ ንግግር የሰሙ ሁሉ ሜክሲካውያንን ከአደንዛዥ እፅ፣ ከአስገድዶ መድፈር እና ሌሎች ወንጀሎች ጋር ያያይዟቸዋል ። በዚህም ምክንያት አንድም ወንጀል ድርጊት ውስጥ ተሳትፎ የሌለው ንፁ ዜጋ ሳይቀር፣ ደርሶ ስርአት አስከባሪ ነው በሚሉ የኚሁ ሰው ተከታዮች ጥቃት የጅምላ ፍርድ ሰለባ ይሆናል ማለት ነው። እሳቸው ወግ አሳምራለሁ፣ ስደተኛ ጠል የሆነውን የማህበረሰብ ክፍል ድምፅ አገኛለሁ በሚል ሊሆን ይችላል እንዲህ ያሉ ንግግሮችን የሚያዘወትሩት። የብዙ የሰው ዘርን ህይወት አደጋ ላይ እየጣሉ መሆኑን ማሰብ ግን አይፈልጉም።

በሀገራችን በኢትዮጵያም ቢሆን በማህበራዊ መገናኛብዙሀን የሚካሄደው በተለይም ብሄር እና ሀይማኖት ላይ ያተኮረው የጥላቻ ንግግር እና ትርክት ምን ያክል ፅንፍ የያዘ እንደሀኖ ለመረዳት ለጥቂት ደቂቃዎች ማህበራዊ መገናኛብዙሀን ላይ መቆየት ይበቃል። አቶ ዝናቡ ቱና የተባሉ፣ የጠቅላይ አቃቤ ህግ የህዝብ ግንኙነት ቢሮ ሃላፊ በ2018 ለአዲስ ስታንዳርድ እንደተናገሩት ኢትዮጵያ ውስጥ እያደገ የመጣ ከጥላቻ ንግግር እና ሳንሱር ከማይደረግ ደርሶ ማህበረሰብ አንቂ ነኝ ባይነት ጋር የተያያዘ ከፍተኛ ስጋት አለ። ጉዳዩም አፋጣኝ የህግ ማእቀፍ ሊበጅለት እና አጥፊዎች እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል።

በመግቢችን ላይ እንደጠቀስነው የጥላቻ ንግግር ዋነኛ አላማ አንድን አካል ጠላት አድርጎ በህዝብ አእምሮ መቅረፅ (በአሜሪካን ሀገር ትራመፕ የሚሰሩትን ስንመለከት ነጭ ያልሆኑ የሰው ዘሮችን እና ስደተኞችን) እና ራስን ከነዚህ ጠላቶች ነፃ የሚያወጣ መሲህ አድርጎ በማቅረብ የምርጫ ድምፅ ማግኘት ነው። ለአጭር ጊዜም ቢሆን ትራምፕ በዚህ ስኬት እንደተጎናፀፉ ማንም ሊክድ አይችልም። የአለማችን ትልቅ ኢኮኖሚ የሆነውን ሀገር ለድፍን አራት አመታት ሊመሩበት ችለዋል፣ በክብር ላይ ክብር ተጎናፅፈውበታል፣ በሀብት ላይ ሀብት አካብተውበታል። የእንቧይ ካብ ሆኖ ሸርተት ቢልና ቢጥላቸውም በአንድ ወቅት በዳመና አስጉዟቸዋል።

በሀገራችንም ቢሆን ጉዳዩ እንዲሁ ነው። በርካቶች የጥላቻ ንግግርን እና ትርክትን እውነት አስመስለው ማጣቀሻ እያቀረቡ ለበርካታ አመታት ሲሰብኩን ኖረዋል። እውነት እንነጋገር ከተባለ የዛሬይቱ ኢትዮጵያዊ እንደ እሳተጎመራ የሚንተገተገው ስሜቱ የሀገር ስሜቱ ሳይሆን የብሄር ስሜቱ ነው። በዚህ ስሜት ውስጥ ሆነን ምርጫ ስናካሂድ ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚገባው ጉዳይ ማንኛውም በጉዳዩ ላይ ተሳታፊ የሆነ የምርጫ ተወዳዳሪ፣ ደጋፊ፣ ማህበረሰብ አንቂ፣ አስመራጭም ሆነ ተመራጭ ከምንም አይነት ከጥላቻ ንግግር ጋር ተያያዥ ከሆኑ ድርጊቶች እና የተግባበት እንቅስቃሴዎች መራቅ አለበት። ይህ ሳይሆን ቢቀር እና ትንሽ የጥላቻ ንግግር ክብሪት ብትለኮስ የሚነደው ሀገር ነው። በረዥም ጊዜ ደግሞ፣ ወደድንም ጠላንም፣ ዘወጥር እየፈራን ሳንነካ የምናልፈው የበርካታዎቹ የጥላቻ ንግግሮች መነሻ የሆነውን እባጭ ከህገመንግስታችን፣ ከታሪክ ትምህርታችን እንዲሁም በዋኝነት ከህዝባችን አእምሮ ውስጥ ለማውጣት ከፍተኛ ባጀት ተመድቦ በማስተማር፣ የህግ ማእከቅ በማበጀት እና በቅጣትም ጭምር ለማጥፋት መስራት ያስፈልጋል። ይህም በብዙ ሀገራት፣ በተለይም እንደ ሩዋንዳ ያሉ ለመስማት እና ለማሰብ የሚቀፍ ታሪክ ገፈት ቀማሽ የሆኑ ሀገራት የተተገበረ ሲሆን፣ እኛም ችግሩን ከነሰንኮፉ ለመንቀል በሩዋንዳ የደረሰው እስኪደርስብን መጠበቅ የለብንም። ፖለቲከኞቻችን እንደ ኢንተር ሀምዌ ያሉ በሩዋንዳው የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ ወቅት ትልቅ የጥፋት ሚና የተጫወተውን ቡድን ስም ለመሰዳደቢያነት ብቻ ከመጠቀም ያለፈ ስራ ሰርተው ታሪክ መቀየር ይኖርባቸዋል። ይህን በአፋጣኝ ማድረግ ካልተቻለ ግን በሀገራችን እያየን ያለናቸው አንዳንድ አጓጉል አደረጃጀቶች ምርጫን የመሰሉ አጋጣሚዎችን ተጠቅመው እንደኢንተር ሀምዌ ያለ ሚና ሊጫወቱ ስላለመቻላቸው እርግጠኛ መሆን አይቻልም።

## 3.2. ምርጫን እና የምርጫን ሂደት ለማስተጓጎል መሳሪያ ሆኖ ማገልገል

ትክክለኛውን የምርጫ ሂደት ተከትሎ መራጩ ህዝብ ድምፁን ለሚያምንበት ተመራጭ ግለሰብም ሆነ ፓርቲ ለመስጠት በመጀመሪያ በምርጫ ማመን አለበት። ዛሬ ላይ በማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን የምናያቸው ዋልታ ረገጥ አስተሳሰቦች ግን ህብረተሰቡ በመሰረቱ በምርጫ እንዳያምን እና ወጥቶ እንዳይመርጥ የሚያግባቡ እና የሚቀሰቅሱ ናቸው። 'እኔ ካልበላሁት ይደፋ' አይነት አመለካከት ያላቸው ፅንፈኛ ብሄርተኞች እና ፖለቲከኞች፣ በዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንደማይሳካላቸው ሲያውቁ፣ ምርጫውን፣ የምርጫውን አስፈፃሚ አካላት፣ የምርጫውን ሂደት እና ተያያዥ ሂደቶች ወደማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን በመሄድ ማጣጣል ይጀምራሉ። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑን የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ዶናልድ ትራምፕ ናቸው። እሳቸው ውድድሩን በሚመሩበት ሰአት እና አካባቢ ድምፅ ቆጠራው እንዲቀጥል እሳቸው በውድድሩ በመሚመሩበት ደግሞ ሰአቱ ሳይደርስ ቆጠራው እንዲቆም ሲጠይቁ የነበሩ ጉደኛ ሰው ናቸው።

ይህንን እኩይ አላማቸውን ለማሳካትም ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀንን ራሳቸውም ደጋፊዎቻቸውም በሰፊው ሲጠቀሙ ነበር። በማንኛውም ሀገር ምርጫ ቢሆን ይህ የተለመደ ሂደት ነው። በምርጫ ወቅት እና ድምፅ ቆጠራ በሚካሄድበት ጊዜ ሊሸነፍ የመሰለው ወገን ወደማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን እየመጣ አንዳች የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት የምርጫውን ተአማኒነት በማጣጣል ነውጥ ማስነሳት ይጀምራል። በዚህም ውስጥ ሀሰተኛ መረጃዎችን ማሰራጨት፣ ዛቻዎች እና ማስፈራሪያዎች በሰፊው አገልግሎት ላይ ይውላሉ።

ይህ እኩይ ምግባር በእያንዳንዱ የምርጫ ሂደት የሚካሄድ ነው የሚሆነው። የመራጮች ምዝገባ መካሄድ ከመጀመሩ በፊት እንኳን በርካታ የከተሞችን የህዝብ አሰፋፈር(demography) በመቀየር ምርጫን ለማሸነፍ ሴራ ተጠንስሷል የሚል ወሬ የማህበራዊ መገናኛብዙሀን ወሬ ማሟሻ ከሆነ ሰንበትበት ብሏል። በምዝገባ፣ በምርጫ፣ በቆጠራ እንዲሁም ውጤት በሚገለፅበት ወቅት ሁሉ የተለያዩ መረጃዎች በማህበራዊ መገናኛብዙሀን በሰፊው እየተሰራጩ ምርጫውን እንደአጠቃላይ ዋጋ ለማሳጣጥ ጥረት መደረጉ አይቀርም። የአካባቢ፣ የክልል እና ሀገራዊ ምርጫ ተወዳዳሪዎች የምርጫ ሂደቱን እና ውጤቶችን በትእግስት መከታተል እንጂ ያልተጨበጠ መረጃ ላይ የተሰረተ የሴራ ትርክት እየፈጠሩ በማህበራዊ መገናኛብዙሀን ከማሰራጨት መቆጠብ አለባቸው። በማንኛውም ወገን ያሉ ደጋፊዎችም እንዲሁ ራሳቸውን ከቡድን አስተሳሰብ ገለል አድርገው ምክንያታዊ በመሆኑ ሂደቱን መከታተል አለባቸው እንጂ የጥፋት ተልእኮ ይዞ በማህበራዊ መገናኛብዙሀን በመደራጀት ለእኩይ ተግባር መሰማራት ሀገርንም ራሳቸውንም አይጠቅምም። እንደአጠቃላለይ በሁሉም የምርጫ ሂደቶች የምራጫውን ተአማኒነት በማውረድ ህዝብ በምርጫው ንቁ ተሳትፎ እንዳያደርግ በውጤቱም እንዳያምን ከፍተኛ ስራ በማህበራዊ መገናኛብዙሀን የሚሰራ መሆኑን

አውቆ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል። ህዝብ በዚህ ሳይደናገር፣ ውጤቱ ምንም ሆነ ምን፣ በምርጫ የመሳተፍ ዴሞክራሲያዊ መብቱን በመጠቀም ሀሳቡን በካርድ መግለፅ አለበት።

## 3.3. ከምርጫ ጋር ተያያዥ የሆኑ ግጭቶችን መቀስቀስ እና ማዛመት

ከምርጫ ጋር የተያያዘ ግጭት አዲስ ነገር አይደለም። ነገር ግን በዛሬ ዘመን የምናየው እየጨመረ የመጣው ተመሳሳይ አስተሳሰብ ካላቸው ሰዎች ጋር ማህበራዊ መገናኛብዙሀን የመገናኘት እድል መልእክቶች ለቁጥጥር አስቸጋሪ በሆነ መንገድ ማስተላለፍ እንዲቻል አድርጓል። ማህበራዊ መገናኛብዙሀን ለዘመናት ሲተላለፉ የኖሩ እና ለግጭት መነሻ የሆኑ የጥላቻ ንግግሮችን መይም ፍረጃዎችን( stereotypes)አልቀየረም ነገር ግን እነዚህ መልእክቶች ህብረተሰቡ ውስጥ ሰርስረው የሚገቡበትን ፍጥነት እና ግለሰቦችንም ሆነ ቡድኖችን ለእኩይ ድርጊት የሚያነሳሱበትን ደረጃ በጣም አሳድጎታል።

በ2007 የኬንያ ምርጫ ምንም እንኳ ማህበራዊ መገናኛብዙሀን በሰፊው ጥቅም ላይ ያልዋለ ቢሆንም፣ በፅሁፍ መልእክት እንኳን ምን ያክል ጥፋት ሊደርስ እንደሚችል ለመታዘብ ተችሏል። ምንም እኳን ኬንያ ከምርጫ ጋር ተያያዥ የሆኑ ግጭቶች ታሪክ ያላት ብትሆንም ያ ወቅት ግን የፅሁፍ መልእከት መጠቀም የተጀመረበት ወቅት በመሆኑ ለየት ያሉ ሁኔታዎች ነበሩ።

ተንቀሳቃሽ ስልክ ሊሰጥ የሚችላቸው ጥቅሞች በተግባር በታየው የጥላቻ ንግግሮችን በፅሁፍ መልእክት የማስተላለፍ እኩይ ተግባር ተሸፈነ። በወቅቱ በተነሱ ግጭቶች ከ1000 ሰዎች በላይ ሲሞቱ ከ500000 ለመፈናቀል ተገደዱ ( ዘ ስታንዳርድ፣ 2008)።

በወቅቱ የወጣው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሪፖርት እንዳሳየው የፅሁፍ መልእከት የጥላቻ ንግግርን ለማስፋፋት በሰፊው ግልጋሎት ላይ ውሏል። ከ2005 የኢትዮጵያ ምርጫም በኋላ መንግስት የፅሁፍ መልእክቶች በመንግስት ላይ የሚካሄዱ ተቃውሞዎችን ለማደራጀት እየዋለ ያለበት መንገድ ስላላማረው አገልግሎቱን ለአንድ አመት ከስድስት ወር ያክል ዘግቶት እንደነበር ይታወሳል።

ዛሬ በርካታ የማህበራዊ መገናኛብዙሀን ብቻ ሳይሆን በነዚህ ውስጥ ተደራጅተው በሰከንድ ውስጥ ሚሊየኖችን ሊያገናኙ የሚችሉ ቡድኖች እና ቻናሎች አሉ። አንዳች እኩይ ምግባር ይዞ የተነሳ የማህበራዊ መገናኛብዙሀን ተጠቃሚ ግጭት ሊያስነሳለት የሚችል የመሰለውን መልእክት ቢያስተላልፍ ምን የክል ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል መገመት ይቻላል። ለዚህም ነው፣ በተለይ በማህበራዊ መገናኛብዙሀን ትልቅ

ተቀባይነት ያላቸው ሰዎች፣ ለተከታዮቻቸው የሚያቃርቧቸውን መልእክቶች በተለይም ከምርጫ እና ከውጤት ጋር ተያይዞ፣ በጣም በጥንቃቄ ሊያርሙ ይገባል የሚባለው። ማንም ቢሆን ከጥቂት ወራት በፊት አሜሪካን ሀገር በተመሳሳይ ሁኔታ ምርጫን ተከትሎ የደረሰው የሰው ህይወት መጥፋት፣ ንብረት መውደም እና የምርጫ እና ዴሞክራሲ ታሪክ መበላሸት እኛም ሀገር እንዲደርስ አይፈልግም። እነሱ እብድ መሪ መርጠው በማህበራዊ መገናኛብዙሀን በሚለቀው የጥላቻ መልእክት ተሳስተው፣ እነሱም መልእክቱን በማህበራዊ መገናኛብዙሀን ተጋርተው የመከራ ገፈት ቀማሽ ሆኑ። ከዚህ ተምረን፣ እነሱ የተሳሳቱትን ስህተት ላለመድገም ከወዲሁ ለህዝብ እና ለሀገር የሚበጀውነ አስቦ በዛ መንገድ ብቻ ለመጓዝ የማህበራዊ መገናኛብዙሀን አጠቃቀማችንን መቃኘት ይገባል።

## 3.4. የምርጫ ውጤት በህዝብ ድምፅ ሳይሆን በተሳሳተ መረጃ ስርጭት ምክንያት እንዲወሰን ማድረግ

ቀደም ባለው ዘመን የምርጫ ተወዳዳሪ የሚሆኑ ፓርቲዎችም ሆኑ ታዋቂ ግለሰቦች ለምርጫ የሚወዳደሩበት ሀሳብ በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ ማሸነፍ የሚችሉት ለህዝብ እና ለሀገር ባደረጉት ትልቅ አስተዋፅኦ እና በሚያካሂዱት ሁሉን አቀፍ በሆነ የምረጡኝ ዘመቻ ነበር። በማህበራዊ መገናኛብዙሀን ዘመን ግን ይህ ሁሉ ማስፈለጉ ጥያቄ ላይ ወድቋል። በግለሰቦች እና በሀገራት መረጃና ደህንነት መስሪያቤቶች በሚሰሩ ማህበራዊ መገናኛብዙሀን ን መሰረት ያደረጉ አንድ ወገን በምርጫው እንዲያሸንፍ ሌላው ደግሞ እንዲሸነፍ የሚያደርጉ የመረጃ ስራዎች ምርጫዎች ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ሲደረግ እንደአንዳንድ የዘርፉ ምሁራን ትንተናም ግለሰቦች እና ፓርቲዎች ከምንም ተነስተው ምርጫን ማሸነፍ ሲችሉ ታይቷል።

ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን የ2016 የአሜሪካ ምርጫ ነው። እንደባለሙያዎች ግምት ሩሲያውያን በዚህ ምርጫ ዶናልድ ትራምፐ እንዲያሸንፉ ይፈልጉ ነበር። ምክንያቱም ሰውየው ከሀገር እና ከህዝብ አንድነት ይልቅ መከፋፈልን፣ በዘር መባላትን የሚሰብኩ፣ ከአለም የዴሞክራሲ ይዘት ይልቅ ገንዘብ የሚበልጥባቸው በመሆናቸው እንደ ሩሲያ ያሉ በዴሞክራሲ አያያዛቸው የሚወቀሱ ሀገራትን እንዲህ አርጉ እንዲያ አታድርጉ በሚል አይነተርኩንም በሚል ነው። ስለዚህም የማህበራዊ መገናኛብዙሀን መረጃን በመሰብሰብ ሰዎች ምን አይነት መረጃ በማህበራዊ መገናኛብዙሀን ቢለቀቅ ምርጫቸውን በሚፈለገው አቅጣጫ ያደርጋሉ የሚሉ በርካታ ጥናቶችን በማሰራት በተደረገ የማህበራዊ መገናኛብዙሀን ጥረት ነው ሰውየው ወደነጩ ቤት የገቡት

ይባላል። ሮይተርስ በቅርቡ እንደዘገበው አሜሪካውያኑ ራሳቸው ይህን እውነታ ተቀብለውታል። የሀገሩ ሴኔት አባላት የሆኑ የሁለቱም አውራ ፓርቲዎች አባላት ሩሲያ በ2016 ምርጫ ላይ ያካሄደቸው ጣልቃ ገብነት ቀደም ሲል ከታሰበው በላይ ከፍተኛ መሆኑን አምነዋል። ይህንንም ያካሄደችው ስልታዊ የሆኑ መረጃዎችን ፈፅሞ በማይጠረጠሩ አካላት በማህበፈራዊ በመልቀቅ አሜሪካውያን በዘር፣ በሀይማኖት እና ፅንፈኛ በሆኑ አስተሳሰቦች እንዲከፋፈሉ በማድረግ ነው።

የማህበራዊ መገናኛብዙሀን አጥኚ የሆነው ኒው ኖውሌጅ፣ እና ኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ግራፊካ ከተባለ የዚሁ ዘርፍ አጥኚ ጋር ሆነው በሰሩት ጥናት ይህንኑ አረጋግጠዋል። እነሱ ባወጡት መረጃም፣ ለአብነት ያክል አንድ የሩሲያ የደህንነት መስሪያቤት አካል በካሊፎርያ እና ቴክሳስ ያሉ የመገንጠል እንቅስቃሴዎችን መረጃ በማህበራዊ መገናኛብዙሀን በማሰራጨት ድጋፍ ማድረጉ ተደርሶበታል። ይህንኑ ተንተርሰውም ሪቻርድ በር የተባሉት የሪፐብሊካን ፓርቲ ተወካይ የሆኑት የሴኔቱ የደህንነት እና መረጃ ኮሚቴ ሰብሳቢ እንዳሉት ይህ መረጃ የሚያሳየን ሩሲያ ምን የክል አሜሪካውያንን በዘር፣ በሀይማኖት እና በአስተሳሰብ ለመከፋፈል እየሰራች እንደሆነች ነው (ኒው ኖውሌጅ፣ 2020)።

ቀጥለውም እንዳሉት የሩሲያ የደህንነት መስሪያ ቤት በአሜሪካ የዴሞክራሲ ተቋማት ያላቸው ተቀባይነት እንዲቀንስ ከፍተኛ ስራ ሲሰራ ቆይቷል ዛሬም እየሰራ ነው። ኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ግራፊካ ከተባለው ድርጅት ጋር ሆነው የሰሩት ጥናትምህ የሚያሳየው ይህንኑ ሲሆን ሩሲያ የተለያዩ ሚስጥራዊ ዘዴዎችን በመጠቀም ግጭት አነሳሽ የሆኑ የሴራ ትርክቶችን እና ሌሎች የራሷን ፍላጎት ለማሳካት የሚያስችሉ የፖለቲካ ዜናዎችን እና የተሳሳቱ መረጃዎችን በመላ ሀገሪቱ ላሉ መራጮች እንዲደርሱ በማድረግ ታሰራጫለች።

በሀገራችንም ቢሆን በርካታ ማህበረሰብ አንቂ የሚባሉ እና ሌሎች በማህበራዊ መገናኛብዙሀን መረጃ በሰፊው ለህዝብ እንዲደርሱ የሚያደርጉ አካላት ከጋዜጠኝነት ስስ መጋረጃ ጀርባ ከማን ጋር እና ለምን አላማ እንደሚሰሩ መታወቅ፣ ስራቸው እና ስራቸው በህዝብ አስተሳሰብ ላይ የሚያሳድረው ተፅእኖ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ጥናት ተደርጎበት፣ የህግ ጥሰት ያለበት እንደሆነ፣ ህጋዊ እርምጃ። ያም ባይሆን መረጃው ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት የሚቀንስ የመፍትሄ እርምጃ መወሰድ አለበት። ሀገራችን፣ እድገቷን የማይመኙ ጠላቶች ያሏት ትልቅ ሀገር ነች። አንደ ግብፅ ያሉ የጥቅም ግጭት አለን ብለው የሚያምኑ ሀገራት ከመጋረጃ ጀርባ ምን ሊሰሩ እንደሚችሉ መገመት አይከብድም። ወጣቱ ትውልድም ቢሆን በምርጫው በንቃት መሳተፍ ብቻ ሳይሆን በየማህበራዊ መገናኛብዙሀን የሚደርሰውን መረጃ በሆደ ሰፊነት መመርመር እና ማጣራት

እንዲሁም በምንም አይነት መልኩ አስተሳሰቡን በነዚህ መረጃዎች ላያ በመመርኮዝ ብቻ መቀየር የለበትም፡ ፡ ከማህበራዊ መገናኛብዙሀን ይልቅ በቤታችን፣ በአካባቢያችን እና በመላ ሀገራችን በኑሯችን የምናውቀው መረጃ በማንኛውም ማህበራዊ መገናኛብዙሀን ከምናገኘው ለውድድር በማይቀርብ መጠን ይበልጣል፡፡ ለምርጫም ሆነ ለሌላ አላማ አስተሳሰባችንን ሊቃኝም የሚገባው እሱ ነው፡፡

## ማጠቃለያ

በዝርዝር ማየት እንደቻልነው ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን እና ምርጫ በዛሬ ዘመን ከፍተኛ የሆነ ትስስር አላቸው፡፡ እንደሰለጠነ ህዝብ ሆነን ከተጠቀምንባቸው ማህበራዊ መገናኛብዙሀን ምርጫ ሲካሄድ በመደበኛ መገናኛ ብዙሀን ከፍተኛ ወጪ ሊያስወጡ የሚችሉ እና አስቸጋሪ የሆኑ የቅስቀሳ እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ቀላል ያደርጋሉ፡፡ ለእኩይ አላማ የዋሉም እንደሆን ማህበረሰቡን በተለይም ወጣቱን በማነሳሳት፣ ለጥፋት በማሰማራት አስከፊ የሆነ ጥፋት ለማድረስ እንደመሳሪያ ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡ ስለዚህም ማህበረሰቡ ይህን ተገንዝቦ በምርጫ ወቅት በዋነኝነት ከሀሰተኛ መረጃ እና ከጥላቻ ንግግር ራሱን ጠብቆ ማህበራዊ መገናኛብዙሀንን በመጠቀም ለምርጫው ስኬት የራሱን አስተዋፅኦ ማበርከት አለበት፡፡ ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ተደራሽ፣ ወጭ ቆጣቢ እና ፈጣን በመሆናቸው ማንኛውንም አሉታዊ ከምርጫ ጋር የተያያዘ 'ውጡና ምረጡ' አይነት መልእክት ለማስተላለፍ ሁነኛ መላ ናቸው፡፡ ለእኩይ አላማ የዋሉም እንደሆን ማህበረሰቡን በተለይም ወጣቱን በማነሳሳት፣ ለጥፋት በማሰማራት አስከፊ የሆነ ጥፋት ለማድረስ እንደመሳሪያ ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ፤ ሲያገለግሉም ታይተዋል፡፡ ለዚህም ነው ሳይቃጠል በቅጠል ነውና፣ ከወዲሁ መልካምን የሚያጎለብት፣ እኩይን የሚያሰናክል ስራ በትጋት መሰራት አለበት የምንለው፡፡

**ማጣቀሻ ፅሁፎች**


Addis Standard November 23, 2018

Boyd, Danah. and Ellison, Nicole (2008). Social network sites: Definition, history, and scholarship. Journal of Computer-Mediated Communication, 13(1), article 11.

Kietzmann et al. (2011). Social Media? Get Serious! Understanding the Functional Building Blocks of Social Media. Indiana university, US

Lyons, Terrence, International Journal of Ethiopian Studies, Vol. 5, No. 1 (Spring/Summer 2010), pp. 107-121, Tsehai Publishers, http://www.jstor.org/stable/41757576, Accessed: 20/06/2014 06:59

Forbes article, Social Media Could Determine The Outcome Of The 2020 Election

Gil de Zuniga, et al.ጊል ደ ዙኒጋ እና ሌሎች፣ 2010

The Standard, 2008

The New Knowledge, 2020